# የታለ ምሁሩ?!

ዲግሪ ይዣለሁኝ፣ ማስተርስ ዶክትሬት
ለስልጣን ልዘጋጅ በአገሬ መሬት
ለዛ ይሆን ማሸርገዱ ይሄ ሁሉ ጋጋታ
ከእኔ በላይ ላሳር በአጓጉል ድንፋታ
ምን ሊጠቅም ይሆን? ኢትዮጵያ ተደፍታ
ቆም ብለህ አስተውል እስቲ ለአንድ አፍታ።

ጐጠኛው ወያኔ አይቀርም መውደቁ
ከቶ ምን ይባላል?ድምፅህን ማጥፋቱ፣ያንተ መደበቁ
መከራውን ሳትካፈል ህዝብን አለሁ ሳትል
የድል አጥቢያ አርበኛ ልትሆን ስትሸሽ ከትግል
ኋላ ያስተዛዝባል አይመች ለግልግል።
ይልቅ ይሻልሃል ብትቆም በክፉ ቀን
ወገንህ ሲገደል፣ ሲኖር በሰቀቀን
አብረህ ስትጋፈጥ ለወገንህ በሙያህ
ያኔ አክብሮ ነው እንደወገን የሚያይህ
ስለዚህ አትጠብቅ ቀን እስኪመቻች
ድምፅህን አሰማ እየፃፍክም ተች።

ከመጣው ጋር ሁሉ ትተህ ማጨብጨብ
ቀሪዋ ኢትዮጵያ ናት አድርጋት ካብ፣ካብ
የፖለቲካ ሽኩቻው በሀሳብ ቢለያይም
አገር ትበልጣለች ይህ አይታበልም
ምን የተማርክ ብትሆን ማዕረግ ብትደረድር
ምንም ዋጋ የለው አገር ጠም ስታድር።

አህምሮክ እንዳይዝግ ስራ በመፍታቱ
ሌሎች ካለዕውቀታቸው ህዝብን ሲያስቱ
ለግል ጥቅማቸው ሲኖሩ እያምታቱ
እንግዲህ ለምን ነው መማርህ ልፋቱ?
ፃፍ፣ፃፍ አድርገህ ህዝቡን ካላስተማርክ
አሽናፊ ሳትጠብቅ ለእውነት ካልመሰከርክ።

ከሚካኤል ሰይፉ (ቶሮንቶ፤ ካናዳ)